የኢትዮጵያ
ኢንተርፕራይዝ ልማት

# የወጪ ንግድና የተኪ ምርት የድጋፍና ክትትል የአሠራር ስርዓት

ሰኔ/2017 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

## ማውጫ ገጽ


መግቢያ ....... 2

ክፍል አንድ ....... 4

ጠቅላላ ትርጓሜ ....... 4

1.1. አጭር ርዕስ ....... 4

1.2. ትርጓሜ ....... 4

1.3. የተፈጻሚነት ወሰን ....... 6

1.4. የተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ድጋፍና ክትትል ኮሚቴ ስለማቋቋም ....... 6

1.5. ዓላማ ....... 6

1.6. አስፈላጊነት ....... 7

1.7. መርሆዎች ....... 8

ክፍል ሁለት ....... 9

የኮሚቴ አባላት አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት ....... 9

2.1. የዓብይ ኮሚቴ አባላት አደረጃጀት ....... 9

2.2. የዓብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ....... 9

2.3. የአብይ ኮሚቴ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት ....... 10

2.4. የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አደረጃጀት ....... 11

2.5. የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት ....... 11

2.6. የሥራ ዲሲፕሊንና ተጠያቂነት፤ ....... 12

2.7. የሥራ ቦታ እና ወጪ ....... 12

2.8. ሚስጥር ጠባቂነት ....... 12

ክፍል ሶስት ....... 13

ሰነዱን ስለማሻሻል ....... 13

## መግቢያ

የኢትዮጵያ የልማት እቅድ ዘላቂ፣ ፈጣን፣ ሰፊ መሰረት ያለውና አካታች የሆነ ከኢኮኖሚ እድገቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ንግድን በማስፋፋት እና የወጪ ምርት አይነቶችና የመዳረሻ ገበያዎችን በማሳደግ የአፍሪካ የብልፅግና ሞዴል መሆን ነው። ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞቻችን ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ምርታማነትን በማሳደግ፣ የማምረት ብቃትን፣ አቅምን እና ተወዳዳሪነትን በማሳደግ እና የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ዘርፍ በማሳት ነው።

በአስር ዓመቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ወጪ ንግድ እቅድ መሰረት በዘመኑ መጨረሻ ከዘርፉ ወጪ ንግድ 9 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለማግኘት እየተሠራ ይገኛል። ይሁን እንጂ እስካሁን በዘርፉ ያለው የወጪ ንግድ አፈጻጸም እድገት ቢኖርም ለአለም አቀፍ የምርቶች ዋጋ መዋዠቅና ተለዋዋጭ ለሆነው ዓለም አቀፋዊ ፖለቲካዊ ግጭት ተጽእኖ አጋልጦታል። ስለሆነም በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ፖሊሲ ማሻሻያ አጀንዳ ላይ በመመስረት ተግዳሮቶችን ለመፍታት በፖሊሲው የሚወሰዱ እርምጃዎችን ከፊሲካል፣ ሞኒተሪ እና የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ጋር በማጣጣም መስራት አስፈላጊ ነው።

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ወጪ ንግድን በማስፋፋት፤ገቢ ምርቶችን በመተካትና የሥራ እድል በመፍጠር፤ የሴቶችን ሥራ ፈጣሪነት እና የልማት ስራ ተሳትፎ በማስፋትና በማስተዋወቅ ረገድ በኢኮኖሚው ውስጥ የላቀ ሚና አላቸው።

ሆኖም ግን ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በአለም አቀፍ ንግድ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ፣ ወደ ውጭ የሚላኩ እና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶች በመተካት ረገድ ያላቸው ድርሻ ከቁጥራቸው እና ለስራ ስምሪት ከሚያደርጉት ጉልህ አስተዋፅዖ አንፃር አነስተኛ ነው።

ስለሆነም ይህንን አፈጻፀም በተደራጀና በተቀናጀ አግባብ በመምራት የላቀ ውጤት ማስመዝገብ አስፈላጊ በመሆኑ ይህን የሚመራ የተቋሙ የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች እንዲሁም ከአስፈጻሚና በባለድርሻ አካላት መካከል ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ስራዎችን በጋራ በማቀድና አፈፃፀሙ የሚገመገምበት፣ ስትራቴጂክ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች የሚተላለፉበት የጋራ ኮሚቴ አደረጃጀት መፍጠር እንዲቻል የአነስተኛና መከከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ድጋፍና ክትትል የአሰራር ሥርዓት ተዘጋጅቷል።

## ራዕይ

"በ2022 በአፍሪካ የተወዳዳሪነት ተምሳሌት የሆነና በአገራችን ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ ያለው የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተገንብቶ ማየት!"

## ተልዕኮ

- *ለዘርፉ ልማት ምቹ ሁኔታን መፍጠር፣*
- *የዘርፉን አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት አቅም መገንባት፣*
- *መሰረተ ልማቶችን ማልማት፣*
- *ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር ማሳደግ፣*
- *የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍን ማስፋፋት ተወዳዳሪ ማድረግ፡፡*

## እሴቶች

- *ታታሪ፣ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሃብት ማፍራት፣*
- *ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን፣*
- *ለተልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት መትጋት፣*
- *የተሳለጠ ቅንጅታዊ አሰራር ማስፈን፣*
- *አዳዲስ አሠራርና ፈጠራን ማበረታታት፣*
- *እድገት፣ ጥራትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ማበረታታት፣*
- *አሳታፊነት፣ ፍትሃዊነትና ተደራሽነትን ማረጋገጥ፣*
- *በአገር ምርት መኩራት፣*
- *ተአማኒ፣ ተደራሽና ወቅታዊ የመረጃ ስርአት መዘርጋት፣*
- *ለማያቋርጥ ለውጥ ዝግጁ መሆን*

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ትርጓሜ

### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ ሰነድ የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ድጋፍና ክትትል የአሠራር ስርዓት ተብሎ ይጠራል።

### 1.2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ሰነድ የቃላት ትርጉም እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

**"ደንብ"**፦ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ለማቋቋም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣው ደንብ ቁጥር 526/2015 ዓ.ም ነው።

**"ዋና ዳይሬክተር"**፦ ማለት የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበላይ ኃላፊ ነው።

**"ማኑፋክቸሪንግ"**፦ማለት ማሽንን፣ መሳሪያን ወይም ጉልበትን በመጠቀም ጥሬ ዕቃ ላይ የቅርጽ፣ የመጠን ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግ የተሻለ ዋጋ ያለው ምርት ማምረት ነው።

**"አነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 11 (አስራ አንድ) እስከ 50 (ሃምሳ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 600,001.00 (ስድስት መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር 10,000,000.00 ሚሊዮን (አስር ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው።

**"መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት ከ 51 (ሃምሳ አንድ) እስከ 100 (መቶ) ቋሚ ሰራተኞች የያዘ እና ከብር 10,000,000.00 ሚሊዮን 1 (አስር ሚሊዮን አንድ) እስከ 90,000,000.00 ሚሊዮን (ዘጠና ሚሊዮን) ጠቅላላ ሐብት ያለው ኢንተርፕራይዝ ነው።

**"ሸቀጥ"** ማለት ወደ አገር በገባበት ሁኔታ ተመልሶ የተላከ ወይም ለውጭ ገበያ እንዲውል የተመረተ ዕቃ ሲሆን ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ለመያዣ፣ ለመጠቅለያ ወይም ለማሸጊያ የሚውለውን ይጨምራል።

**"ወደ ውጭ መላክ"** ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ ሸቀጦችን መላክ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣዎች ላይ ሸቀጦችን መጫንን ይጨምራል።

**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

**ማኑፋክቸሪንግ ላኪ ኢንተርፕራይዞች፡-** ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በቀጣይነት ወይም በተወሰነ ወቅት ልዩነት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ኢንተርፕራይዝ ነው።

**"የተኪ ምርት ስተራቴጂ"** የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት እና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ከሌሎች ስልቶች እና ፓሊሲዎች ጋር በማይጣረስ መልኩ ስተራቴጂካዊ የተኪ ምርቶችን ማሳደጊያ ስልቶችን በተመረጡ ምርቶች እና ኢንዱስትሪዎች ላይ የጊዜ ገደብ ያለው የመንግስት የማበረታቻና ድጋፍ ማስተግበሪያ አንድ የኢንዱስትሪያላይዜሽን ስልት ነው።

**"ተኪ ምርት" ማለት ፡-** ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን በዋጋ፣ በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት ለመተካት በሀገር ውስጥ የተመረተ ምርት ማለት ነው፡፡

**ዓብይ ኮሚቴ፡-** በተቋሙ የበላይ አመራር የሚሰየም የተኪና ወጪ ምርቶችን እቅድ አፈጻፀም እየመገመ የሚመራ አካል ነው።

**ቴክኒክ ኮሚቴ፡-** ተጠሪነቱ ለዓብይ ኮሚቴ የሆነና የተኪና ወጪ ምርት እቅድ አፈጻጸም እየገመገመ ሪፖርት የሚያቀርብ፤ አቅጣጫ የሚቀበልና የሚያስፈጽም ከተቋሙ ከተለያዩ የሥራ ዘርፎች የተውጣጡ ሰራተኞችን ያካተተ ነው።

**ክትትልና ድጋፍ፡-** የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዝ ዘርፉን የለውጥ አፈፃፀም በሚመለከት የቀረቡ ግብአቶችን፣ የተከናወኑ ተግባራትን የተገኙ ውጤቶችን በመተንተን፣ በመመዝገብና አጠቃላይ አዝማሚያውን በማገናዘብ አፈጻጸሙ ወደታቀደለት አጠቃላይ ስኬት እያመራ መሆኑን የምናረጋግጥበትና የታዩ ክፍተቶችን በመለየት በጋራና በተናጠል መፍትሄ የሚቀመጥበትና የሚፈፀምበት ሂደት ነው።

## 1.3. የተፈጻሚነት ወሰን

በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት፣ በሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች በዘርፉ ባሉ አደረጃጀቶች፣ በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዞች እና በፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የሚሰሩና የሚተገበር ይሆናል።

## 1.4. የተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ድጋፍና ክትትል ኮሚቴ ስለማቋቋም

የተቋሙ የበላይ አመራሮችና ተኪና ወጪ ምርት ማምረት ላይ የተሰማሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከሚደግፉ የሥራ ክፍሎች በተውጣጡ አባላት የሚቋቋም ይሆናል።

## 1.5. ዓላማ

የተኪና ወጪ ምርት የሚያመርቱ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነታቸውን በማሳደግ አገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነታቸውን ማረጋገጥ ነው።

### 1.5.1. ዝርዝር ዓላማ

- የተኪና ወጪ ምርት የሚያመርቱ አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተሟላ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ።
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የማምረት አቅም፣ ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ማሳደግ።
- ከውጪ የሚገባ ምርትን በማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት እና በማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የሚገኘውን የውጪ ምንዛሬ ገቢ መጠንና ድርሻ ማሳደግ፣
- ኢንተርፕራይዞችን በአህገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እሴት ሰንሰለቶች (GVC) ውስጥ ትስስራቸውን ማቀናጀት።
- በሁለትዮሽ፣ በአህጉራዊና ቀጠናዊ አጋርነት እና በባለብዙ ወገን የንግድ ስምምነቶች ለኢትዮጵያ ምርትና አገልግሎት የገበያ መዳረሻ እድል መፍጠር።
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን የዲጂታል ተጠቃሚነት በማሳደግ ምርቶቻቸውን በዲጂታል ተደያዥነት ላላቸው ዓለም አቀፍ የገበያ ቦታዎች ቀርበው በቀላል፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ይበልጥ ግልጽ በሆነ ውድድር እንዲሸጡ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

- በተኪና ወጪ ምርት ስራ ላይ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን እንዲለዩ በማድረግ፤ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርአት በመዘርጋት የተሳለጠ የመረጃ አያያዝ ስርአት መፍጠር፤

## 1.6. አስፈላጊነት

- የ10 ዓመት አነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተኪና ወጪ ምርት የዕቅድ አፈጻጸም ዝቅተኛና የንግድ ሚዛን ጉድለት ከፍተኛ በመሆኑ የንግድ ሚዛን ለማመጣጠን፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የኢኮኖሚ ድርሻና ፋይዳ በግልጽ ያልተቀመጠ ስለሆነ ፋይዳውንና ድርሻውን በጉልህ ለማስቀመጥ፣
- የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራዞችን አቅም በማሳደግ እና ከውጭ በሚገቡት ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት በመቀነስ ብሎም የኢንተርፕራይዞችን ወጪ ንግድ አፈጻጸም ከፍ ለማድረግ፣
  - እንደ ተቋም ወጪ ንግድና ተኪ ምርት የሚመራብት መንገድ ሰፊ ክፍተት ያለበት መሆኑ፣ የተሻለ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ክፍተቶችን መሙላት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

## 1.7. መርሆዎች

- የአሰራር ስርዓቱ በአገር አቀፍ ደረጃ የአምራች ኢንተርፕራይዞችን ተኪና ወጪ ምርት ንግድ ማነቆዎችን ለመፍታት ከተቋቋሙ አደረጃጀቶች ጋር በተናበበ መልኩ እንዲከናወን ይሆናል
- የኮሚቴው ስራ በመደኛ ሁኔታ ያልተሸፋና ስትራቴጂያው ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል፣
- ስራው ግልጽና ተጠያቂነት ባለው አግባብ ይመራል፤
- የኮሚቴው አባላት በከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነትና ዲሲፕሊን ስራውን እንዲመሩ ይደረጋል፤
- የተግባርና ኃላፊነት ድግግሞሽን ባስቀረና ተቋማዊ አቅም ግንባታን መሰረት ባደረገ አግባብ ይፈጸማል፤
- የአሰራር ስርዓቱ ከሚመለከታቸው ከዘርፍ አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤

# ክፍል ሁለት

## የኮሚቴ አባላት አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

### 2.1. የዓብይ ኮሚቴ አባላት አደረጃጀት

በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ደረጃ የሚቋቋመው የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ድጋፍና ክትትል አፈጻጸም በመገምገም ለቴክኒክ ኮሚቴ ግብረ መልስና የመፍትሔ አቅጣጫዎች የሚሰጡ የተቋሙ የበላይ አመራሮችንና መሪ ሥራ አስፈጻሚ አባላት በመያዝ የተዋቀረ አደረጃጀት ሲሆን የአባላቱ ብዛት እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል።

1. የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር..................................ሰብሳቢ
2. የአቅም ግንባታና ፋሲሊቴሽን ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር..........................ም/ሰብሳቢ
3. የኢንቨስመንት ፕሮሞሽንና የገበያ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ.....................ፀሐፊ
4. የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ም/ዋና ዳይሬክተር.................አባል
5. የአግሮ ፕሮሰሲንግ መሪ ሥራ አስፈጻሚ..............................................አባል
6. የኢንጅነሪንግ ውጤቶች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ..........................................አባል
7. የጨርቃ ጨርትና ቆዳ ውጤቶች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ...................................አባል
8. የአቅም ግንባታ መሪ ስራ አስፈጻሚ.....................................................አባል
9. የመሰረተ ልማት፣ ግብአትና ፋይናንስ ድጋፍ መሪ ስራ አስፈጻሚ.....................አባል

### 2.2. የዓብይ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ዓብይ ኮሚቴዎች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

- የዓብይና ቴክኒክ ኮሚቴዎች መሰየም፣ሲንደል መተካት፤
- ዓመታዊ የተኪ እና ወጪ ምርት እቅድ ማጽደቅ፤
- ተኪ ምርትና በወጪ ንግድ ስራ ለማሳለጥ በተፈጠሩ አሠራርና አደረጃጀት ዙሪያ ለሚመለከታቸው አካላት ግልፀኝነት መፍጠር፤
- በቴክኒክ ኮሚቴ የተከናውኑ ሥራዎች ወር በገባ በአምስተኛው ቀን መገምገም፣ ግብረ መልስ መስጠት፤ተፈጻሚነቱን ክትትልና ድጋፍ መከታተል ማድረግ፤የውሳኔና የመፍትሄና ቀጣይ አቅጣጫ ማስቀመጥ፣

- ተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፐራይዞች የሚጋጥሟቸውን ማነቆዎች በተቀናጀ አግባብ መፍታት፣ እንዲፈታ ማድረግ፣
- ተኪና ወጪ ምርት አፈጻጸም በዘላቂነት ማሳደግ የሚያስችል ተቋማዊ ስርዓት መዘርጋት፣
- ተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፐራይዞች ድጋፍና ክትትል ስራ ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አሰራር እንዲዘረጋ ማድረግ፣ ውጤታማነታቸውን መከታተል፣ክፍተት ሲኖር ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግ፣
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፐራይዝ ተኪ ምርትና ወጪ ንግድ ማነቆዎችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፣
- ይህ የአሰራር ስርአት ወደ ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች እንዲሰፋ ማድረግ፣

## 2.3. የአብይ ኮሚቴ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

የአብይ ኮሚቴው ፀሐፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል።

- የዓብይ ኮሚቴ በሚያስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የስብሰባ ፕሮግራም ማውጣት፣
- የቴክኒክ ኮሚቴ ሪፖርት በወቅቱ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ክትትል ማድረግ፣
- የስብሰባ አጀንዳ ማሰባሰብ፣ ለዓብይ ኮሚቴ መሰብሰቢያ አዳራሽን ጨምሮ እና ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፣
- የስብሰባውን ቃለ ጉባኤ ማዘጋጀት፣ ማስፈረምና ለኮሚቴው አባላት ስብሰባው በተካሄደ ሶስተኛ ቀን ድረስ ማስራጨት፣
- ዓብይ ኮሚቴ ያስቀመጣቸውን አቅጣጫዎች ለሚመለከታቸው የኮሚቴ አባላትና የሥራ ክፍሎች በዝርዝር ማሳወቅ፣

## 2.4. የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት አደረጃጀት

የአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች የተኪ ምርትና ወጪ ንግድ የአፈጻጸም ክፍተት በመለየት ድጋፍና ክትትል የሚያድርጉ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ የተቋሙ ከፍተኛ አመራሮችና መካከለኛ አመራሮች ያካተተ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት በመያዝ የተዋቀረ አደረጃጀት ሲሆን የአባላቱ ብዛት እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

1. የአግሮ ፕሮሰሲንግ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ……………………………………ሰብሳቢ
2. የኢንቨስመንት ፕሮሞሽንና የገበያ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ……………ም/ሰብሳቢ
3. የገበያ ልማት ዴስክ ኃላፊ…………………………………………………………ፀሐፊ
4. የመሰረተ ልማት ዴስክ ኃላፊ……………………………………………………አባል
5. የብድርና ሊዝ ፋይናንስ ዴስክ ኃላፊ……………………………………………አባል
6. የኢንተርፕራይዝ አገልግሎትና ሽግግር ዴስክ ኃላፊ……………………………አባል
7. የኬሚካልና ኬሚካል ውጤቶች ዴስክ ኃላፊ………………………………………አባል
8. የምግብ ፕሮሰሲንግ ዴስክ ኃላፊ……………………………………………………አባል
9. የመጠጥ ፕሮሰሲንግ ዴስክ ኃላፊ……………………………………………………አባል
10. የብረታ ብረት ሥራዎች ዴስክ ኃላፊ ………………………………………………አባል
11. የኮንስትራክሽን ግብዓትና የእንጨት ውጤቶች ዴስክ ኃላፊ………………………አባል
12. የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ሥራዎች ዴስክ ኃላፊ…………………………………አባል
13. የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዴስክ ኃላፊ …………………………………………………አባል
14. የግብአት ዴስክ ኃላፊ ……………………………………………………………………አባል

## 2.5. የቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የቴክኒክ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

- የቴክኒክ ኮሚቴውን የሚመራበትን ዝርዝር እቅድ በየንዑስ ዘርፉ ያቅዳል፤
- የተኪና ወጪ ንግድ ዕቅድ ላይ ለኢንተርፕራይዞች ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ኢንተርፕራይዞችን ዕቅድ ያሳቅዳል፤
- ተወዳዳሪነትና ውጤታማነት ላይ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮች በመለየት የጥናት ሥራዎችን ያከናውናል፤

- ኢንተርፕራይዞችን ሊደግፍፍ የሚያስችል የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ለውጤታማነቱ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።
- ተኪና ወጪ ንግድ ምርት ላይ ግንዛቤ ለማስፋት አገራዊ የንቅናቄ መድረክ ያዘጋጃል፣
- የምርት ጥራት፣ ተወዳደሪነትን እና ምርታማነት ማሻሻያ ዕቅድ በማዘጋጀት ደረጃ ያልወጣላቸውው ምርቶች ደረጃ እንዲወጣላቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል።
- በምርት ሂደት፣በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር የድጋፍና ምክር አገልገሎት ይሰጣል ፤ ተኪ እና የወጪ ንግድ ምርቶችን ይለያል።
- የሀገር ውስጥ የምርት ዕድገት እና የንግድ ሚዛን የሚያሻሽሉ ቴክኒኮችን ተግባራዊ ለማድረግ ከማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች፣አስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይሠራል።
- ተኪና ወጪ ምርት የሚያመርቱ ማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞችን በመለየት በልዩ ሁኔታ ስታንዳርዱን የጠበቀ የመሰረተ-ልማት፣ የማምረቻ፣ ማሳያና መሸጫ ማዕከላት፣ የፋይናንስ፣ የግብዓት፣ ቴክኖሊጂና ገበያ ትስስር ቅድሚያ የሚያገኙበት ሁኔታ ያመቻቻል፣
- ኢንተርፕራይዞች እርስ በእርስና ከከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ ከሌሎች ተቋማትና ድርጅቶች በገበያ የሚተሳሰሩበትን ሥርዓት መቀየስና ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፤
- በየ15 ቀኑ ክክልልና ከተማ አስተዳዳሮች በተኪ ምርትና ኤክስፖርት ምርት ዘሪያ የተሰሩ ስራዎችን ሪፖርት በጋራ መገምገም፣
- ተኪ ምርትና ወጪ ንግድ እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ወር በገባ በሶስተኛው ቀን መገምገም፤ በአራተኛው ቀን ለአብይ ኮሚቴ ሪፖርት ገምግሞ ማቅረብ፤
- ዓብይ ኮሚቴው የሚያስቀምጣዎችን አቅጣጫዎች መተግብር ናቸው።

## 2.6. የሥራ ዲሲፒሊንና ተጠያቂነት፤

ህግና ስርዓት ተከትሎ ተግባራትን የማይፈፅም የኮሚቴው አባል ተጠያቂ ይሆናል።

## 2.7. የሥራ ቦታ እና ወጪ

የኮሚቴው የሥራ ቦታ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ይሆናል። ለሥራው የሚውል ወጪ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማትና የልማት አጋር መስሪያ ቤቶች በሚገኝ ገቢ የሚሸፍን ይሆናል።

## 2.8. ሚስጥር ጠባቂነት

ዓብይም ሆነ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ማንኛውንም ተቋሙን ሊጎዱ የሚችሉ መረጃዎችን ሚስጢራዊነት የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው።

# ክፍል ሶስት

# ሰነዱን ስለማሻሻል

ይህ ሰነድ በአስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የማያሠራ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበላይ አመራሮች ጋር ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፤

## 3.1. ሰነዱ ጋር የሚቃረን አሰራር

ከዚህ አሰራር ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሂደት በዚህ ሰነድ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

## 3.2. የሰነድ ስርጭት

የፀደቀው ሰነድ በሀትመት፣በኦንላይ ክትሮኒክ እና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል።

## 3.3. ሰነዱ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ሰነድ ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ማኔጅመንት ቀርቦ ከጸደቀበት ከ------ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

**ዶክተር አለባቸው ንጉሴ**

***የኢትዮጵያ የኢንተርፕራይዝል ልማት ዋና ዳይሬክተር***

# ክፍል ሶስት

## ሰነዱን ስለማሻሻል

ይህ ሰነድ በአስፈጻሚና ባለድርሻ አካላት የማያሠራ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የበላይ አመራሮች ጋር ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፤

### 3.1. ሰነዱ ጋር የሚቃረን አሰራር

ከዚህ አሰራር ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሂደት በዚህ ሰነድ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

### 3.2. የሰነድ ስርጭት

የፀደቀው ሰነድ በህትመት፣በኦንላይ ክትሮኒክ እና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል።

### 3.3. ሰነዱ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ሰነድ ለኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ማኔጅመንት ቀርቦ ከጸደቀበት ከ------ ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ዶክተር አለባቸው ንጉሴ

*የኢትዮጵያ የኢንተርፕራይዝል ልማት ዋና ዳይሬክተር*